COLORADO
Department of Regulatory Agencies
Colorado Civil Rights Division

# የኮሎራዶ ሕግ መኖሪያ ቤትን የሚመለከት አድልዎን

# ይከለክላል

C.R.S. § 24-34-501 et seq.

## ቀጥሎ ያለው አድሏዊ ወይም ኢፍትሐዊ የመኖሪያ ቤት አሰራር ነው፡

ማንኛውም ሰው ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ለሌላ ሰው ቤት ለማሳየት፣ ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ፣ ለማከራየት ወይም በሊዝ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን ወይም በቅን ልቡና የቀረበለትን ቤት የመግዛት፣ የመሸጥ፣ የማከራየት ወይም በሊዝ የመስጠት ጥያቄን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን ወይም ቤትን ዝግጁ አለማድረግ ወይም መከልከል ወይም ይዞ ማስቀረት፤ ወይም ከማንኛውም የቤት አገልግሎት ጋር በተያያዙ ደንቦች፣ ሁኔታዎች ወይም ልዩ መብቶች ላይ ልዩነት ማድረግ የለበትም።

## ምክንያቶች፡

የአካል ጉዳት፣ ዘር፣ ቀለም፣ ፆታ፣ ወሲባዊ ዝንባሌ (ፆታ የቀየሩትን ጨምሮ)፣ ሃይማኖት፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የቤተሰብ ሁኔታ፣ ብሔራዊ አመጣጥ ወይም ዝርያ ወይም የገቢ ምንጭ*

---

## ለአካል ጉዳተኞች የሚሆን ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው መኖሪያ ቤት፡

አካል ጉዳት ያለበት ሰው የተሟላና እኩል የሆነ የቤት ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስፈልገውን ምክንያታዊ የሆነ መኖሪያ ቤት እና/ማሻሻያ የማግኘት መብት አለው። አንድ መኖሪያ ቤት ያልተገባ የፋይናንስና አስተዳደራዊ ጫና የሚያስከትል አቅርቦት ካለው ወይም የቤት አቅራቢው ስራ ላይ መሰረታዊ ለውጥ የሚያስከትል ከሆነ ምክንያታዊ አይደለም ማለት ነው።

---

## አገልግሎት ሰጪ እንስሳት፡

ድጋፍ ሰጪ እንስሳት የሚባሉት አገልግሎት ሰጪ እንስሳትና ስሜታዊ ድጋፍ የሚሰጡ እንስሳትን የሚጨምር ሲሆን፣ በቤት ውስጥ ምክንያታዊ አገልግሎት መስጫ አንዱ መንገድ ነው። አካል ጉዳተኛ የሆነ ሰው የቤት እንስሳትን የማይፈቅድ ፖሊሲ ወይም ድጋፍ ሰጪ እንስሳቶቻቸው በእነርሱ ቤት ውስጥ አብረው እንዳይኖሩ የሚከለክል ፖሊሲ እንደ ምክንያታዊ ማረፊያ ቦታ ሊጠይቅ ይችላል።

አገልግሎት ሰጪ እንስሳት የሚባሉት የተወሰነ ተግባር እንዲፈጽሙ ወይም ከአካል ጉዳት ጋር የተያያዘ ስራ እንዲሰሩ በተናጠል የሰለጠኑ ውሾች ወይም ግልገል ፈረሶች ናቸው። ዓይነ ስውር መሪ ውሻ ወይም የጤና ሁኔታ ማስጠንቀቂያ ሰጪ ውሻ እንደ ምሳሌ ይጠቀሳሉ።

ስሜታዊ ድጋፍ የሚሰጡ እንስሳት የአእምሮ ጤና ችግርን ለማቃለል የሚያስችሉ የቴራፒ ድጋፍ የሚሰጡ ማናቸውም እንስሳት ሊሆኑ ይችላሉ።

---

## ብቀላ የተከለከለ ነው፡

አድሎአዊ አሰራርን የሚቃወም ወይም የአድሎአዊነት ምርመራ፣ ሒደት ወይም ችሎት ውስጥ የተሳተፈ ሰው ላይ የብቀላ እርምጃ መውሰድ አድሏዊ ተግባር ነው።

---

## የ2020 CROWN Act፡

በዘር ላይ የተመሰረተ አድሎ የፀጉር ልስላሴ ወይም መሻከር፣ የፀጉር አይነት ወይም በተለምዶ ወይም በታሪክ ከዘር ጋር የሚያያዝ የፀጉር አሰራር፤ ለምሳሌ ሹርባ፣ ሎክስ፣ ትዊስትስ፣ ታይት ኮይል ወይም ከርል፣ ኮርንራውስ፣ ባንቱ ኖትስ፣ አፍሮ እና ፀጉርን ጠቅልሎ ማሰርን ይጨምራል። ተግባራዊ የሚሆንበት ቀን፡ 9/13/20።

EQUAL HOUSING OPPORTUNITY

**CCRD ፍትሐዊ የሆነ የቤት ድጋፍ ፕሮግራም (FHAP) ሲሆን፣ ፍትሐዊ የቤት አገልግሎት ሕጎችን በማስፈጸም ሒደት ውስጥ ከ HUD ጋር በትብብር ይሰራል**

**አድሎ ተፈጽሟል የሚል ቅሬታ ለማቅረብ፣ ወይም ለተጨማሪ መረጃ፣ የኮሎራዶ የሲቪል መብቶች መምሪያን በቀጣዩ አድራሻ ያነጋግሩ፡ 1560 BROADWAY, LOBBY WELCOME CENTER, SUITE # 110, DENVER, CO 80202**

**ዋና ስልክ ቁጥር፡** 303-894-2997፤ **ስፓኒሽ ሆትላይን፡** 720-432-4294፤ **ከክፍያ ነጻ፡** 800-262-4845፤ V/TTD **RELAY፡** 711፤

**ፋክስ** 303-894-7830፤ **ኢሜይል፡** DORA_CCRD@STATE.CO.US

**ከመኖሪያ ቤት ጋር የተያያዙ አድሏዊነትን የሚመለከቱ ቅሬታዎች ተፈጸመ የተባለው የአድሏዊነት ተግባር በተፈጸመ በአንድ (1) ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት።**

*ተግባራዊ የሚሆንበት ቀን፡ 1/1/21